# ውትድርና?!
## በሚሊዮን ደሳለኝ ሰማኝ

ጥበበ የዕለት ሥራውን በሚገባ አጠናቅቆ ወዳመሻሹ ላይ ወደ ቤቱ መጓዝ ጀመረ። ጥቂት እንደተጓዘም በሕልሙ ያየውን ጉዳይ አስቦ ያሰላስል ጀመር። «የሚገርም ሕልም ነው። ሰው ወታደርነትን ለማምለጥ እግሬ አውጪኝ ይላል እኔ ወታደር ካልሆንኩ ብዬ ደጅ ጥናት! ብቻ በተለምዶ እንደሚባለው ሕልም የዕውን ግልባጭ ነው ይሉ የለ? እንዴ ... ታዲያ ሊጠሩኝ እኮ ይሆናል! ይሄኔ ነው መሸሽ አሉ! ለነገሩ እኔን እንኳን አይጠሩኝም ሌላው ቢቀር እድሜዬ ገፍቷል።

«ብቻ ሰው ከጠፋ ... የሚሉት ነገር አለ አሉ። ይህንንም ሰው ነገረኝ እንጂ እርግጠኛ አይደለሁም። ነገር ግን ብጠራስ? እኔ እንኳን ግድ የለኝም ... እናቴ ግን ሰው የምትሆን አይመስለኝም። ለነገሩ እኔስ ብሆን መች አየሁት? የጦር ሜዳ ጀግንነት መቼም ከሲኒማው የአቡጀርዲድ ዘመቻ እጅጉን የተለየ መሆን አለበት። የዕውነት ነዋ! ግንእኮ በሲኒማውም ውስጥ ቢሆን የሰዎቹ አይሁን እንጂ እጅና እግር ተፈናጥሮ ከዋናው አካሉ ሲለይ እናይ የለም! ደመና ይመስል የሚትጎለጎለው እሳትና ጢስ፥ እንኳን እንደኔ ያለውን ኮስማና ቀርቶ ተራራ ሲያከስል ያሳዩናል።

«ወቸ ጉድ እንዲያው ካልጠፋ ሃሳብ የጦር ሜዳ ጉዳይ ሲንጠኝ ያምሽ እንዴ? ቆይ ... ግን ብጠራስ? ምንድን ነው የማደርገው? እርግጠኛ ነኝ ... በመጀመሪያ ይችን የሳሳች ጠጉሬን ይላጩአታል። ከዚያ እንደ ከረጢት ያለ ልብስ ሰጥተው የለበስኩትን ያስወልቁኛል። ስሮጥ እግሬ እንዳይላላጥ ብቻ ጫማ በልኬ እንደሚሰጡኝ ተስፋ አደርጋለሁ። ከአንድ ከሦስት ቀን የበረሃ ውጣ ውረድ በኋላ እንኳን እናቴ እኔም መልኬን በመስተዋት ባየው የማውቀው አይመስለኝም። በቴሌቪዥን የማያቸው ወታደሮች ከአንድ እናት ከአንድ አባት የተወለዱ ይመስል መልካቸው አንድ አይነት ነው። ልዩነታቸው በውስጥ ባህርያቸው ብቻ ይመስለኛል። ነጭናጫው ያው ነጭናጫ ነው፣ ተጫዋቹ በሞት ሳይቀር ይቀልዳል፣ ድብርታሙም እንኳን ቅጠልያ ለብሶ ጸሐይ እየከካው፥ በአገር ደህናም ድብርታም ነው። ያ ሁሉ ሆኖ ግን ለአንድ ድምጽ ይታዘዛሉ የሚታዘዙትን ለመፈጸምም እስከ ሞት ድረስ ራሳቸውን ሰጥተዋል።

«ታድያ ... እኔ ወታደር ነኝ የምል ከሆነ የተመለመልኩ ዕለት ነዋ እናቴ ልታለቅስ የሚገባት። የምሞተው እኮ የዛ ዕለት ነው። ከዚያ በኋላ ያለውን ጊዜ በተንቀሳቃሽ አስከሬንነት ነው የማሳልፈው። ለካስ ሰው አንድ ጊዜ ለውትድርና ራሱን ሲሰጥ ሙት ነው። የኔ የሚለውን መብቱን ሁሉ የሚያስረክበው በዚያን ቀን ነው። ከዚያ በኋላማ ተኛ ሲባል ይተኛል፣ ተነስ ሲባል ይነሳል፣ ሩጥ ሲባል ይሮጣል፣ ብላ ሲባል ይበላል፣ ጩህ ሲባል ይጮሃል፣ ዝም በል ሲባል ጸጥ ይላል። ምን መልበስ እንዳለበት፣ እንዴት መቆም እንዳለበት ሌላው ቀርቶ የትኛው እግሩ መቼ መሬት እንደሚረግጥ አዛዡን በማዳመጥ እንደተባለው ብቻ ያደርጋል እንጂ አንዳች በራሱ ፈቃድ አይከውንም።

«አዛዡ በሚሰጠው ቃል መሠረት ሂድ ሲባል ይሄዳል። ተዋጋ ሲባል ይዋጋል። ሞትን አይቶ የማይፈራት ለካስ ቀድሞ ስለሞተ ነው። መብቴ ለሚለው ነገር፥ የኔ ለሚባል ነገር ሙት ነው። እዚህ አድርጉኝ ብሎ አይከራከርም። ለነገሩ

መብቱም የለውም። አዛዡ ብቁ ነው ላለው ነገር ይታመናል። በታዘዘ ጊዜ ይህ ለምን ሆነ አይልም "እሺ ጌታዬ!" ብሎ ሰላምታ ሰጥቶ አመስግኖ ያከናውናል። በማዕበል ውስጥ ሲላተም፣ በጦር ወላፈን ውስጥ ሲያልፍ፣ እርግጠኛ መሆን የሚፈልገው አዛዡ ከቅርቡ መኖሩንና ድምፁን በትክክል መስማት መቻሉን ብቻ ነው። የሚቀጥለው ተግባር ምን እንደሆነ ሳይሰማ አይንቀሳቀስም።

«ለካስ አንድን ሰው ወታደር የሚያደርገው የሚለብሰው መለዮ አይደለማ! ነገር ግን ከዚያ ሁሉ በፊት፣ ከመሰልጠኑም በፊት፣ መሳሪያ ከመጨበጡም በፊት፣ ለውጊያ ብቁ ነህ ከመባሉም በፊት ለመሞት ፈቃደኛ መሆኑ ነው። ለፈቃዱ መሞት አለበት፣ ለነዚህ ብቻ አይደለም ለብዙ ነገሮች መሞት አለበት።»

ጥበበ ለራሱ ውትድርናን የሚያስተምር ይመስላል። ከዚያ በፊት ስራዬ ብሎ ስለዚህ ጉዳይ አስቦ አያውቅም ነበር። በአጭር ጊዜ ውስጥ የውትድርናን ዓለ ም መዳሰሱ ለራሱ ገረመው። ይልቁንም ውትድርና የመስዋዕትነት ሕይወት እንጂ የራስ ሕይወት አለመሆኑን ሲረዳ፣ በውትድርና ውስጥ መስማት ያለበት ድምፅ አንድ ብቻ መሆኑን ሲያሰላስል፣ ባለፈው እሁድ የሰንበት ትምሕርት ሲማር፣ ሃዋርያው ጳውሎስ ከአንድም ሁለት ቦታ «ከክርስቶስ ጋር ተሰቅያለሁ ።» ስላለው ቃል የተማረው ትውስ አለው።

«እውነትም ወታደር ከወታደርም ጀነራል!» አለ ጳውሎስን አስቦ። «በዕውነት ጳውሎስ ለራሱ ያልሞተ ቢሆን ኖሮ ያን ሁሉ መከራ ይችል ነበር? በድንጋይ ተወገረ፣ የመርከብ አደጋ ደረሰበት፤ እፉኝት ነደፈው፣ ከአህጉር አህጉር ተንከራተተ፣ በበሽታ ተሰቃየ፣ ያልታሰረበት ዓይነት ወህኒ - ያልተገረፈው ዓይነት ግርፋት አልነበረም።

«አዛዡ ሂድ ሲለው የሚሄድ፣ ቁም ሲለው ደግሞ የሚቆም፣ ዕለት ዕለት ድ ምጹን በመስማት የሚታዘዝ፣ በደህናው ቀን የተማረውን የውትድርና ዝማሬ በመከራ ቀን በማስታወስ የመሬት መንቀጥቀጥን ያስከተለ ታማኝ ወታደር ጳውሎስ፣ ለካ ገና ድሮ ውትድርናን አውቆት ኖሯል። ውትድርና እንግዲህ ... ከአንደኛው ሞቶ ለአንደኛው ሕያው የመሆን ምስጢር መሆኑ ነው። እኔም ታድያ የተመለመልኩ ዕለት ነዋ ለራሴና ለእናቴ የምሞተው፣ ልታዘዘው የወደድኩት አዛዤ የሚያውቀኝ ደግሞ የዛኑ ዕለት መሆኑ ነው። አይገርምም?

«ታድያ እኮ ጳውሎስም "ከክርስቶስ ጋር ተሰቅያለሁ እኔም አሁን ሕያው ሆኜ አልኖርም ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል፤ አሁንም በስጋ የምኖርበት ኑሮ በወደደ ኝና ስለ እኔ ራሱን በሰጠው በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለ እምነት የምኖረው ነው። (ገላትያ 2፥19-20)" ማለቱ ይህ ዛሬ ለእኔ የተገለጠልኝ ሕይወት ለእርሱ በጊዜው ግልጥ እንደነበረለት የሚመሰክር ነው።

«ይልቁንም በወደደኝና ስለ እኔ ራሱን በሰጠው የሚለው ቃል በዚያ ሰሞን ያነበብኩትን የጦር መኮንን ታሪክ የበለጠ አስደናቂ ያደርግልኛል። እኔ እንደዚያ መኮንን የማሰለጥናቸው ሰዎች ቢኖሩና ጠላት አድብቶ ቦንብ ቢወረውርብን፣ ሌሎቹ ወታደሮቼ በሕይወት እንዲኖሩ ቦንቡን እንደ ኳስ ቀልቤ በመሬት ላይ በመደፋት ሌሎችን ለማትረፍ ብቻዬን እንድሞት እፈቅድ ይሆን? አላውቅም። መኮንኑ ግን፣ ለመሞቱ እርግጠኛ ነበር። ሌሎቹን ለማትረፉም እርግጠኛ ነበር። የወሰደው እርምጃ ቅጽበታዊ አይመስልም። «ይህ ቢሆን ...» ብሎ የተዘጋጀ ራሱን ለመስዋእትነት አሳልፎ ለመስጠት ከቆረጠ ሰው ብቻ

ሊሆን የሚችልን ነገር አደረገ። ይገርማል።

«ከሞት ጋር ፊት ለፊት መፋጠጥ፥ ሲታሰብም የሚያስደነግጥ ነው። በሞትና በሕይወት መካከል መቆም፥ ምን አይነት ስሜት ያስከትል ይሆን? ብቻ ቀደም ብሎ ለሞተ ለውጡ ብዙ ላይሆን ይችላል። ቢሆንም ግን … እንዲህ አድርጌ ላምለጥ ብሎ ከማሰብ ይልቅ እኔ ጠፍቼ ሌሎችን ላትርፍ። ድንቅ መሰጠትን ይጠይቃል። ለነገሩ … ያ መኮንን ያስተማረን ግን … ምን አይነት ፍቅር ነው?!»

ጥበበ ይህን በምናቡ የሚጎበኘውን የውትድርና ሕይወትና ራሱን ሰውቶ ለሌሎች መዳን የሆነውን መኮንን ጉዳይ ሲያሰላስል ሌላ እውነት እንደገና በራለት። ያ የተደነቀበት መኮንን ያደረገው ታላቅ ተጋድሎ ቀደም ሲል እጅግ በጎላ ሁኔታ በጌታ ኢየሱስ መደረጉን አስታወሰ። ጌታ ኢየሱስ እኛ ሁሉ በሕይወት እንድንኖር ራሱን ለሁላችን ቤዛ አድርጎ መስጠቱን፣ ሞትን ድል ነስቶ ነፃ እንዳወጣን፣ ለመዳናችን እርሱን ብቻ የምንታመን እኛ ከዘላለም ሞት በእርሱ ሞት እንዳመለጥን፣ እርሱ ሰላማችን በመሆኑ በእኛና በእግዚአብሔር መካከል ያለውን የጠብ ግድግዳ አፍርሶ ርቀን ለነበርነው ለእኛ የእግዚአብሔር ልጆች የመሆንን ስልጣን እንዳስጨበጠን አስተዋለ።

«ድንቅ ልዑል ጀነራል።» አለ ሳያስበው። «አሳንሼህ ከሆነ ይቅር በለኝ ጌታ ሆይ! ለኔ ግን ድንቅ ልዑል ጀነራል ነህ የእግዚአብሔር ልጅ ጌታ ኢየሱስ። እኔም ዛሬ ለእኔ ሞቻለሁ ከእንግዲህ እኔ ወታደርህ አንተም አዛዤ ትሆናለህ።» ብሎ ቃል ገባ።

ለኔ ርስቴ ኢየሱስ ነው
ለኔ ርስቴ ኢየሱስ ነው
ለኔስ ግብ ዓላማዬ … እርሱን ማስከበሬ
በዚህች በምድር ላይ … ስሙን ማስጠራቴ
ኑሮ የምለው ይህን ነው … ኑሮ የምለው ይህን ነው
ከዚህማ ሌላ ኑሮ የሞት ሞት ነው
ከዚህማ ሌላ ሕይወት ጨለማ ነው።

ጥበበ ወደ ቤቱ ሲያዘግም ወደ መዳረሻው ላይ እናቱ ነጠላቸውን አዘቅዝቀው ከለቅሶ ቤት ሲመጡ አገኛቸው። ትንሽ አረፍ ካሉ በኋላ እርሱም እንዴት እንደሞተና እንዴት ደግሞ ሕያው እንደሆነ ሊያጫውታቸው አሰበ።

እንዴት ያለ ግሩም ምሽት
በመሞት ሕይወት የሚገኝበት።